የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

**Veterinary drug and animal feed Administration and control authority**

# የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መሳሪያዎች አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥና ቁጥጥር መመሪያ

01/2006

ታሕሳስ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

መግቢያ ....................4
ክፍልአንድ ....................5
አጠቃላይ ....................5
1. አጭር ርዕስ ....................5
2. ትርጓሜ ....................5
3. የተፈፃሚነት ወሰን ....................6
4. ዓላማ ....................6
ክፍልሁለት ....................7
የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ....................7
5. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ....................7
6. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይዘት ....................8
7. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማሳደስ ....................8
8. የአድራሻ፣ የባለቤትነት፣ የባለሙያ ወይም የደረጃ ለዉጥ ....................9
9. ስለምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ....................9
10. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚቀመጥበት ቦታ ....................10
ክፍል ሦስት ....................10
ዲዛይንና አስፈላጊ ግብአቶች ....................10
11. የአካባቢ ሁኔታ ....................10
2. የማከማቻ ክፍል ዲዛይን ሁኔታ ....................12
3. አስፈላጊ ግብዓቶችና ቁሳቁሶች ....................12
ክፍልአራት ....................13
የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ ....................13
13. የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ ....................13
14. ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎች ....................14
15. የባለሙያው ኃላፊነትና ግዴታ ....................14
ክፍል አምስት ....................16
የእንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ ስለማስመጣት፣ ስለመላክ፣ ግዥናሽያጭ ....................16
16. እንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት የሕክምና መሣሪያ ስለማስመጣት ....................16
18. የእንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ ግዢና ሽያጭ ....................17
ክፍል ስድስት ....................18
ስለ እንስሳት መድኃኒትና የእንስሳት ሕክምና መሣሪያዎች አከመቻቸትና አያያዝ ስርዓት 18
19. ስለ አከመቻቸትና የአያያዝ ስርዓት ....................18

20. ነፃ ናሙና ....................................................................................19
21. ስለ መዝገብ አያያዝና ሪፖርት አደራረግ ....................................................20
ክፍል ሰባት .......................................................................................21
አስተዳደራዊ እርምጃዎች .......................................................................21
22. በጠቅላላው .......................................................................................21
23. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማገድ .........................................21
24. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ ......................................23
25. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እገዳና ስረዛን ስለማንሳት ......................24
26. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመመለስ ......................................24
27. የእንስሳት መድኃኒትና የእንስሳት ሕክምና መሣሪያን ስለማስተላለፍ ...............24
28. ስለ ቅሬታ አቀራረብ ..........................................................................25
ክፍል ስምንት .....................................................................................25
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ..............................................................................25
29. መረጃን ይፋ ስለማድረግ ....................................................................25
30. የአግልግሎት ክፍያ ............................................................................26
31. ተፈፃሚ ስለማይሆኑ ሕጎች ..................................................................26
32. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ ..................................................................27
ዕዝል1… ...........................................................................................27
ዕዝል 2 ..............................................................................................31
ዕዝል 3 ..............................................................................................35

## መግቢያ

የእንስሳት መድኃኒትናየሕክምና መሣሪያዎችጥራታቸዉን፤ፈዋሽነታቸዉንናደህንነታቸዉን ሊያጡና ሊለወጡ ይችላሉ፡፡ በዚህም ምክንያት በሰዉና በእንስሳት ሕይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርሱ ስለሚችሉ ከጥሬ ዕቃ ዝግጅት ጀምሮ በአመራረት፤ በክምችት አያያዝ፤በማስመጣት፤በማከፋፈልና በሚላክበት ወቅት አስፈላጊዉ ጥንቃቄና ክትትል መደረግ አለበት፡፡ከዚህ አንፃርየእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መሣሪያ የማስመጣት፣ በጅምላ የማከፋፈልና የመላክ ተግባር አግባብነት ባለዉ ባለሙያ እንዲሁምመስፈርቱን ባሟላ ተቋምእንዲከናወን ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

በዚህም መሠረት የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥርን ውጤታማ በሆነ መልኩ ሥርዓት ማስያዝ አስፈላጊ በመሆኑ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጥር ወር በቁጥር 728/2004 ባወጣው አዋጅ መሠረት የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 272/2005ተቋቁሟል፡፡

በመሆኑምደህንነቱ፣ ጥራቱና ፈዋሽነቱ የተጠበቀ የእንስሳት መድኃኒትና የእንስሳት ህክምና መሣሪያዎችን አቅርቦትና አጠቃቀም ቁጥጥርን በማሻሻል የእንስሳት ሀብት ልማትንና ጤንነት አጠባበቅን በማሳደግ ረገድ ባለስልጣኑ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ያስችለው ዘንድየእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሣሪያዎች አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶችን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥና ቁጥጥር በሚመለከት በአዋጅ ቁጥር728/2004 አንቀፅ 28 ንኡስ አንቀፅ 2 በተሠጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍልአንድ

## አጠቃላይ

## 1. አጭርርዕስ

ይህ መመሪያ "የእንስሳትመድኃኒትናየእንስሳትሕክምናመሣሪያ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥና ቁጥጥርመመሪያ ቁጥር 01/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የእንስሳት መድኃኒትና መኖአስተዳደርናቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 728/2004ዓ.ምአንቀፅ 2 ስር ለተቀመጡቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡-

1. "ባለስልጣን" ማለት የእንስሳትመድኃኒትናመኖ አስተዳደርናቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡
2. "እገዳ" ማለት ማንኛውም በእንስሳት መድኃኒትናየእንስሳት ሕክምና መሣሪያ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ባለስልጣኑያወጣዉን የቁጥጥር መመሪያ በመጣሱ ወይም ባለማክበሩ ምክንያት ከሶስት ወር እስከ አንድ አመት ለሚሆን ጊዜ ስራውን እንዲያቋርጥ የማድረግአስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ፡፡
3. "ስረዛ" ማለት ማንኛውም በእንስሳት መድኃኒትና በእንስሳትሕክምና መገልገያ መሣሪያ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ባለስልጣኑያወጣዉን የቁጥጥር መመሪያ በመጣሱ ወይም ባለማክበሩ ምክንያት ከሁለት አመት ለማያንስ ጊዜ ስራውን እንዳይሰራ የማድረግ አስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ፡፡
4. "ተንቀሳቃሽ ሽያጭ" ማለት ያለ ገኘሮው የፅሁፍ፣የፋክስ፣የኢ-ሜይል ጥያቄ ውጪ የመድኃኒት ሽያጭ ማከናወን ነው፡፡
5. "ድርጅት" ማለትበእንስሳት መድኃኒት ወይምየእንስሳት ህክምና መሣሪያ ማስመጣት ወይም ጅምላ ማከፋፈል ወይምበመላክ ንግድ ስራ ላይ የተሠማራ የንግድ ተቋም ማለት ነው፡፡

6. "ተቆጣጣሪ" ማለት በእንስሳት መድኃኒት ወይም በእንስሳት ህክምና መሣሪያ ንግድ ላይ የተሰማራን ነጋዴ መመሪያዎችን እንዲሁም በባለስልጣኑ የወጡ መመዘኛዎን አክብሮ መስራቱን የሚቆጣጠር የባለስልጣኑ ሠራተኛ ነው፡፡
7. "ነጻ ናሙና"ማለት አንድ የእንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ ንግድ የሚያከናውን ነጋዴ የምርቶቹን ጥራት ለማረጋገጥ በላብራቶሪ ፈተሸ የሚደረግለት ወይም ለማስተዋወቅ በነጻ ለተጠቃሚዎች የሚያሰራጫቸው የእንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት ሕክምና መሣሪያዎች ናቸው፡፡
8. "አግባብ ያለው አካል" ማለት እንደ አገባቡ የንግድ ሚኒስቴር ወይም ማንኛውም የሙያ ስራ ፈቃድ ለመስጠት ስልጣን ያለው አካል ማለት ነው፡፡

## 3. የተፈፃሚነትወሰን

ይህ መመሪያበመላው ሀገሪቱ ለተቋቋመና አዲስ ለሚቋቋም ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ አስመጪ፣ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ወይም ላኪ ድርጅት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ፡

1. የእንስሳት መድኃኒትና የእንስሳትሕክምና መሣሪያ ንግድ ድርጅት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆንና ብቃትና ሙያዊ ስነምግባር ባለዉ ባለሙያ ስራው እንዲከናወንማድረግ ነዉ፡፡
2. ሕብረተሰቡ ደህንነቱ፣ ጥራቱና ፈዋሽነቱ የተጠበቀና የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒትናየእንስሳት ሕክምና መሣሪያ እንዲያገኝ ነው፡፡
3. የእንስሳት ምርትና ምርታማነት እንዲያድግና ጤናማ የእንስሳት ተዋፅኦ ለተጠቃሚው ህብረተሠብ እንዲቀርብ ማስቻል፡፡

## ክፍልሁለት
## የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀት

### 5. የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀትአሰጣጥ

1. ማንኛዉምየእንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት ሕክምናመሣሪያ አስመጪ ወይም ላኪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት ከባለስልጣኑየብቃትማረጋገጫምስክርወረቀትሳያገኝ መሥራት አይችልም ፡፡
2. ማንኛዉም ሰው የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀት ለማግኘት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፣

ሀ. በባለሥልጣኑ በተዘጋጀዉ ቅጽ ማመልከቻ ሞልቶማቅረብ፣

ለ.ሌሎች አግባብነት ያላቸዉ በባለስልጣኑየሚወጡ መስፈርቶችን ማሟላት

ሐ.አስፈላጊዉን የአገልግሎት ክፍያ መክፈል ፡፡

3. የቀረበው ማመልከቻ የተሟላ ከሆነ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትየጠየቀዉድርጅትከሁለት እስከ ሦስትአባላትባሉት የባለስልጣኑ የተቋማት ምዝገባና ፍቃድ ሙያተኞች ቡድንእንዲታይ ይደረጋል፡፡
4. አመልካቹ የተሟላ ማመልከቻ ካላቀረበማመልከቻዉን በድጋሚ አስተካክሎ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
5. በባለስልጣኑ የተቋማት ምዝገባና ፍቃድ ባለሙያዎችየተሞላዉ የመገምገሚያ ቅፅከተቀመጡት መመዘኛዎች አኳያ በባለሥልጣኑ□ባ□ ሀላ□□ች ተፅምፅሞ እ□ናትቅ □□ረ□ል፡፡
6. አመልካቹ መስፈርቶቹን አሟልቶ ካልተገኘ ባለስልጣኑ ሊሟሉ የሚገባቸዉን ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳዉቀዋል፡፡
7. አመልካቹ ማሟላት ያለበትን ሁኔታዎች እንዲያሟላ በጽሁፍ ተገልጾለት በዚሁም መሠረት አሟልቶ ካቀረበ ተገቢዉን ክፍያ እንዲከፍል ተደርጎ በድጋሚበሙያተኞች ቡድን ድርጅቱ እንዲታይ ይደረጋል፡፡ነገር ግን በተደጋጋሚ ከሁለት ጊዜ በላይ ታ□ቶለት ሳጸሟላ ከቀረ ከሶስት ወር በ□ትሊታይለት አይችልም፡፡

8. የመገምገሚያ ሪፖርቱ በሁሉም ተቆጣጣሪዎች ተፈርሞና ከድርጅቱ ህጋዊ ሠነድ ጋርተያይዞ በባለስልጣኑ በሚገኘው የድርጅቱ ማህደር ዉስጥ መቀመጥ አለበት ፡፡
9. አመልካቹ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ሂደቶች ማጠናቀቁን በተገቢዉ የባለስልጣኑ አካልከተረጋገጠ በኃላ ባሉት ሦስት የስራ ቀናት ዉስጥ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱይሰጠዋል፡፡
10. ባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጥያቄን የማይቀበል ከሆነ ለአመልካቹ ምክንያቱን ገልጾ በጽሁፍ ያሳዉቀዋል፡፡

## 6. የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀትይዘት

በዚህ መመሪያ መሰረት የሚሰጥ ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡-

1) የድርጅቱ ባለቤት ስም፤
2) የድርጅቱን ሥራ በበላይነት የሚመራው ባለሙያ ስምና የሙያ ምዝገባ ፈቃድ ቁጥር፣
3) የድርጅቱ ስምና አድራሻ
4) የድርጅቱ አይነት
5) ድርጅቱ የሚሰጠዉ አገልግሎት
6) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠበት፤የሚታደስበትንና የአገልግሎት ጊዜዉ የሚያበቃበት ቀን፤
7) የሰጠዉ የሥራ ሀላፊ ፊርማና የባለስልጣኑ ማህተም
8) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቁጥር፤
9) በፈቃዱ ላይ የሚሰፍሩ ዝርዝር ሁኔታዎች ወይም ማሳሰቢያዎች፡፡

## 7. የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀትስለማሳደስ

1. ማንኛዉም ሰውየተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትሊያሳድስ የሚችለዉ

ሀ. የምስክር ወረቀቱ በዚህ መመሪያ መሠረት ካልታገደ፣

ለ. የምስክር ወረቀቱ በዚህ መመሪያ መሠረት ካልተሰረዘ፤

ሐ. ድርጅቱ በራሱ ፈቃድ ስራዉን ካላቋረጠ ብቻይሆናል፡፡

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉየብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትየሚታደሰዉ፡-

ሀ.የበጀት ዓመቱ በገባ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ተከታታይ ወራት (ሐምሌና ነሐሴ)፣ ብቻ ሆኖ

ለ.በባለስልጣኑ የወጡ የብቃት መመዘኛዎች፤ደንቦችና መመሪያዎች በድርጅቱየተጠበቁ መሆናቸውንበተቆጣጣሪዎችዓመታዊ የቁጥጥር ሪፖርት ወይም ኢንስፔክሽን ሲረጋገጥእና

ሐ. ተገቢዉ የአገልግሎት ክፍያሲፈፅም ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ)ስርበተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ውስጥ የምስክር ወረቀቱ ያላደሰ ድርጅት እድሳት ላላደረገባቸው ለእያንዳንዱሁለት ተከታታይወራትመስከረም እና ጥቅምት የእድሳት ክፍያውን ዋጋ ሃምሳ በመቶ ተጨማሪ ቅጣት በመክፈል እንዲታደስለት መጠየቅ ይችላል፡፡ ነገር ግን ከሁለት ወራት በኃላ የምስክር ወረቀቱን እንዲያድስ አይፈቀድለትም፡፡

4. ምስክር ወረቀቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (3)መሠረት ሣይታደስ ከቀረ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፣

5. ባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕድሣት ማመልከቻ ጥያቄን የማይቀበል ከሆነለአመልካቹ ምክንያቱን በፅሁፍ ጸሳዉቃል፡፡

## 8. የአድራሻ፣የባለቤትነት፣የባለሙያወይምየደረጃለዉጥ

ማንኛዉምሰዉ ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ የአድራሻ ወይም የባለቤትነት ወይም የባለሙያእንዲሁም የድርጅቱን ደረጃ ለዉጥ ወይምየመጋዘን ጥገና ወይምየክፍሎች ለዉጥ ወይምሽግሽግ እና ክፍፍል ማካሄድ አይችልም፡፡

## 9. ስለምትክየብቃትማረጋገጫምስክርወረቀት

1. ማንኛዉም ድርጅት የተሰጠዉ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትየጠፋበት ወይም የተበላሸበት ከሆነ ምትክ የማግኘት መብት አለዉ፡፡

2. ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት የሚቻለው ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተዉ ሲገኙ ብቻ ነዉ፡፡

ሀ. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የጠፋበት ከሆነ የምስክር ወረቀቱ የጠፋበት ስለመሆኑ የሚገልፅ ማስረጃ አግባብነት ካለዉ የፍትህ አካል በጽሁፍ ሲያቀርብ ወይም

ለ. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተበላሸበት ድርጅት ከሆነ፣የተበላሸዉን የምስክርወረቀት ለተገቢዉ አካልሲመልስ እና

ሐ. አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ ሲከፍል፡፡

## 10. የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀትየሚቀመጥበትቦታ

1. ማንኛውም ድርጅትበባለስልጣኑ የተሰጠውን ዋናዉን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለእይታ በሚያመች እና ግልጽ በሆነ ቦታ በድርጅቱ መገልገያ ሕንጻ ግድግዳ ላይ ሁልጊዜ ማንጠልጠልይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን የሚጻረር ተግባር ፈጽሞ በተገኘ ድርጅት ላይ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2እና 3 መሠረት ባለስልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

# ክፍልሦስት

## ዲዛይንናአስፈላጊግብአቶች

## 11. የአካባቢሁኔታ

1. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒትናየእንስሳት ሕክምናመሣሪያንግድድርጅት የሚቋቋምበት አካባቢቀጥሎ የተዘረዘሩትንሁኔታዎች ያሟላመሆን አለበት፤

ሀ. ከሰው መኖርያ ቤት የተለየ፣

ለ.ከእንስሳት መድኃኒት ወይም ከእንስሳት ሕክምና መሣሪያ ንግድሥራየተለየ መትኃኒቱን ዓ ራትና ህንነት ሊለዉጓ ከሚችልሌላ ሥራ የማይሠራበት አካባቢየሆነ፣

ሐ. አካባቢዉ ከቆሻሻ ማከማቻ ቁሶች የጸዳና ከሕዝብ መፀዳጃ ቤት ቢያንስ 100 ሜትርየራቀ፣

መ. ንፅህናዉ የተጠበቀ ሆኖ ብክለት ሊያስከትሉ ከሚችሉ ከጎርፍና ከመሰልተዛማጅ ቆሻሻዎች እንዲሁም የመድኃኒት ባህርይን ሊለዉጡ ከሚችሉ ማናቸዉም ነገሮችጽዱየሆነ፣

ሠ. የተሟላየመሰረተ ልማትአውታሮች እንደ መብራት ዉሃና የቴሌኮሙኒኬሽን መገናኛዎች የተሟሉለት፡፡

2. በማንኛዉምየእንስሳት መድኃኒትናየእንስሳትሕክምና መሣሪያ ንግድ ድርጅትግቢዉስጥ ራሳቸዉን ችለዉ የተከፋፈሉ፣

ሀ. የማከማቻ ክፍል፣

ለ. የመረካከቢያ ክፍል፣

ሐ. የቴክኒክ ኃላፊ ቢሮ፣

መ.የእጅ መታጠቢያዉሃ ያለውየመጸዳጃ ክፍልሊኖሩትይገባል፡፡

## 12. የማከማቻ ክፍሎች አሠራርየዲዛይን ሁኔታና አስፈላጊ ግብዓቶችና ቁሳቁሶች

### 1. የማከማቻክፍሎች አሠራር

ሀ. ግድግዳዉ ከድንጋይ፤ ከብሎኬት ወይም ከሸክላ የተሰራና ሊታጠብበሚችል ቀለም የተቀባ፣

ለ. የጣሪያው ኮርኒስ ከጨርቅ ወይም ከማዳበሪያ የተሰራ፣

ሐ. ወለሉ ከሲሚንቶ፤ ከጣውላ ወይም ከሸክላ የተሰራ፣

መ. ክፍሎቹ በቂ ብርሃን ሊያስገቡ የሚችሉ፣በቂ የአየር ዝውውር ያላቸዉና ቀጥተኛ የፀሐይ ብርሃን የማያስገቡ፣

ሠ. የናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች □ሚ□□ ከሆነየሚቀመጡበትየሚቆለፍ ካቢኔት ወይም ክፍል ያለው፣

ረ. መጋዘኑ የሚቆለፍ በር ያለዉና በተጨማሪም ከማንኛዉም በራሪ ነፍሳት፣ቆርጣሚዎች፣ ተሳቢ ነፍሳት የተጠበቀ፣

ሰ. የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው የእንስሳት መድኃኒቶች ወይም የእንስሳትየሕክምናመሣሪያዎች ወይም ከገበያ የወጡ ምርቶች ተለይተዉ የሚቀመጡበት የተለየ በቂ ቦታ ወይም ክፍል ያለው፣

ሸ. ለመርዛማና ተቀጣጣይ መድሀኒቶች የተለየ ቦታያለውሊሆን ይገባል፡፡

## 2. የማከማቻ ክፍልዲዛይንሁኔታ

በዚህአንቀፅስርየተቀመጡድንጋጌዎችእደተጠበቁሆነውየእንስሳትመድኃኒትና የእንስሳትህክምናመሳሪያማከማቻዲዛይንሁኔታበዚህመመሪያአዝል(3)ላይበተቀመ ጠውንድፈምስል(lay-out)መሰረትመሆንአለበት።

## 3. አስፈላጊግብዓቶችናቁሳቁሶች

1. ማንኛዉም የእንስሳትመድኃኒትና የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ ንግድ ድርጅትየሚከተሉት ለአሰራሩ አስፈላጊ ግብዓቶች ሊኖሩት ይገባል፡፡
   - ሀ. መድኃኒቱ በመደርደሪያየሚቀመጥ ከሆነ ከግድግዳዉ 20 ሳ.ሜ ርቆ መቀመጥ አለበት፤
   - ለ. መድኃኒቱበፓሌት የሚቀመጥ ከሆነ ፓሌቱከወለሉ10ሳ.ሜ ከፍታ ያለው መሆን አለበት፤
2. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒትና የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ ንግድ ድርጅት የሚከተሉት አስፈላጊ ቁሳቁሶች ሊኖሩት ይገባል፡፡
   - ሀ. ድርጅቱ የናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶችንየሚይዝ ከሆነ ባለቁልፍ ቁምሳጥን ወይም ካቢኔት፤
   - ለ.ድርጅቱ የቅዝቃዜሰንሰለታቸውእንዲጠበቅላቸው የሚያስፈልጋቸው መድኃኒቶችን የሚይዝከሆነ እንደ አግባብነቱ የቅዝቃዜሰንሰለትመጠበቂያ መሣሪያዎችከነሙቀት መቆጣጠሪያው ቴርሞ ሜትር፤
   - ሐ. የግድግዳ ሙቀት መቆጣጠሪያ ቴርሞ ሜትር፤
   - መ. ከፍተኛሙቀት ባለባቸው አካባቢዎች መድኃኒት ያለባቸውክፍሎችን በሚያዳርስ መልኩየአየር ኮንዲሽነር ወይም ቬንትሌተር፤

ሠ. የእርጥበት መለኪያ መሣሪያ፤

ረ. የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ ፤

ሸ. ለመረጃአያያዝ የሚሆንባለቁልፍካቢኔት፤

ቀ. የማደያ ጠረጴዛ፤

በ. በዚህ ንዑስ አንቀፅ ቁጥር 2 (ለ) ድንጋጌመሰረት ሊስተናገዱ የሚገባቸውንመድኃኒቶች የሚይዝ ከሆነ መብራት ሲቋረጥ የሚተካውጄኔሬተር፤

ተ. ስቶክእና ቢን ካርድ፤

ቸ. የቆሻሻ ማጠራቀሚያ፤

ኘ.ለፅዳት አገልግሎት የሚውል የእጅ ጓንት፣የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ መሳሪያ መኖር አለባቸው፡፡

## ክፍልአራት
## የእንስሳትመድኃኒትባለሙያ

የእንስሳትመድኃኒትናየእንስሳትሕክምናመሣሪያንግድድርጅትየሙያፍቃድየተሰጠዉየእንስሳትመድኃኒትባለሙያበሌለበትሥራዉንሊያካሂድአይችልም፡፡በመሆኑምማንኛውምባለሙያፈቃድማውጣትየሚችለውየሚከተሉትንሁኔታዎችአሟልቶሲገኝብቻነው፡፡

## 13. የትምህርትዝግጅትናየሥራልምድ

ሀ.የእንስሳት መድኃኒትና እንስሳት የሕክምና መሳሪያ ንግድ ስራውን በቴክኒክ ኃላፊነት የሚመራው ባለሙያ የእንስሳት ሀኪም ወይም የእንስሳት ጤና ፋርማሲስት ወይም በእንስሳት ህክምና ቢ...ኤስ.ሲ (BSc.) ድግሪ ያለው ሆኖ በባለስልጣኑ የተመዘገበና ለእንስሳት ሀኪም፣ በሙያዉ አንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ያገለገለ፣ እና ለእንስሳት ጤና ፋርማሲስት ወይም ለእንስሳት ህክምና ቢ.ኤስ.ሲ (BSc.) በሙያዉ ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይያገለገለ መሆን አለበት፡፡

ለ. ረዳት የቴክኒክ ባለሙያ (የመጋዘን ኃላፊ) ሆኖ የሚሰራው ረዳት የእንስሳት ሀኪም፣ የእንስሳት ጤና ድራጊስት ወይም የእንስሳት ጤና ፋርማሲ

ቴክኒሽያን የሆነና በሙያዉምሁለትዓመትና ከዚያ በላይ ያገለገለ መሆን አለበት፡፡

ሐ. በዚህ አንቀፅንዑስ አንቀፅ (ለ) □ተቶለ□□ □እን□ተ□በቀ ሆኖ ከዚያ በላ□ □ሙጸ □ረጽ ጸላቸዉ ባለሙጸ□ችም መሳተአ □ችላሉ:

## 14. ሌሎችአስፈላጊሁኔታዎች

ሀ. ባለሙያው ሕግን በመተላለፍበሙያው እንዳይሰራ ያልተከለከለ፣

ለ. የሙያ ግዴታን ለመወጣት የማያስችል የአዕምሮ ሕመም ወይም የአካል ጉድለት የሌለበት ወይም በአልኮል መጠጥ፣ በናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችንእና በሌሎች አደንዛዥ እፆች ሱሰኛ ያልሆነ፣

ሐ. ቀድሞ ይሰራበት ከነበረው መስሪያ ቤት የስራ መልቀቂያ ያቀረበ፣

መ. ቀድሞ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በስሙ ያወጣከሆነ ምስክር ወረቀቱ የመለሰ፣

ሠ.በረዳትነት በዘርፉ ይሰራ ከነበረ አግባብ ካለውአካል የስራ ልምድ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡

## 15. የባለሙያውኃላፊነትናግዴታ

1. ማንኛዉምበእንስሳትመድኃኒትና በእንስሳትሕክምናመሣሪያንግድድርጅትውስጥበቴክኒክኃላፊነትየሚሠራባለሙያቀ ጥሎየተዘረዘሩትኃላፊነትናግዴታዎችአሉበት፤

ሀ. የተሰጠውን ስራ በራሱ የማከናወን ሀላፊነት

ለ. ባለሙያዉ በማይኖረበት ጊዜ ባለስልጣኑን በማስፈቀድተመሳሳይ የሙያደረጃ፣ አ ቃትናተመሳሳይ የአገልግሎት ጊዜ ያለዉንባለሙያ ከሦስት ወር ላልበለጠ ጊዜተክቶእንዲሰራሊያደርግ ይችላል፣

ሐ. በዉክልና ወቅት ስለተካውባለሙያ ሙሉ መረጃ የመያዝ፣

መ. ከድርጅቱ አስተዳደር ጋር ቀጥታ ግንኙነት በማድረግበድርጅቱ ክፍሎች በመግባት ከአገልግሎት አሰጣጡ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን መቆጣጠር፣

ሠ.ስለ እያንዳንዱ ባለሙያ የስራ ድርሻና ኃላፊነት የሚገልጽ ሰነድ ማዘጋጀት፣

ረ. ባለሙያዎቹ የእንስሳት መድኃኒትና የእንስሳትሕክምና መሣሪያ ጥራትና ደህንነትን በሚመለከት ተጨማሪ ክህሎት ሊያገኙየሚችሉበትን ስልጠናዎች እንዲያገኙ የማድረግ፣

ሰ.የሚወጡ አገር አቀፍ ደረጃዎችንና መመሪያዎችን የመተግበርና የማስተግበር፣

ሸ. የክምችት ክፍሉን ቁጥጥር በተመለከተበተገቢዉ መንገድ መከናወኑን የማረጋገጥ፣

ቀ.የማከማቻና የመደርደሪያዎችን ቦታዎችን ለሚያፀዳ ሰዉ ሊያጋጥሙት ስለሚችሉ አደጋዎች የማሳወቅ፣

በ. የናርኮቲክና የሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች የሚከማቹበት ክፍል የሚቆለፍና በአንድ ባለሙያ ኃላፊነት ሥር መሆኑን ማረጋገጥ፣

ተ. የባለስልጣኑን መመሪያዎች መሰረት በማድረግ ጥቅም ላይ የማይውሉ መድሀኒቶች ወይም የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች በጊዜውና በአግባቡ እንዲወገዱ የማድረግ፣

ቸ. ድርጅቱን የሚለቅ ከሆነ ከመልቀቁ አንድ ወር በፊት ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

2. ከቴክኒክ ኃላፊነት ዉጭ በሌላ ኃላፊነት ላይ የሚሠሩ ባለሙያዎች ኃላፊነትና ግዴታ

ሀ. በድርጅቱ ውስጥ በተሰጠው የስራ ድርሻ መሰረት አገልግሎት የመስጠት፣

ለ.ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን በማግኘትና በቀጣይ ትምህርት፣ስልጠናዎችና ምዘናዎች ራሱን ብቁ የማድረግ፣

ሐ.በማረካከቢያና በክምችት ክፍል ዉስጥመብላት፣መጠጣት፣ሲጃራማጨስ ወይም ሌሎች ንፅህናቸዉ ያልተጠበቁና አላስፈላጊ ተግባራትን አለማከናወን፣

መ. ተገቢ የሆነየስራ ልብስ መልበስ እና የግል ንፅሕናን መጠበቅ፣

ሠ. ማንነቱን፣ ሙያዉንና የስራ ድርሻዉን የሚገልፅ የደረት ባጅ የማድረግ፣

# ክፍልአምስት

## የእንስሳትመድኃኒትወይምየእንስሳትሕክምናመሣሪያስለማስመጣት፣ስለመላክ ፣ግዥናሽያጭ

## 16. እንስሳትመድኃኒትወይምየእንስሳትየሕክምናመሣሪያስለማስመጣት

1. ማንኛዉም የእንስሳት መድኃኒትና የእንስሳት ህክምና መሳሪያ አስመጪድርጅትየእንስሳትመድኃኒት ወይም የእንስሳት ሕክምናመሣሪያ ከዉጭ አገር ለማስመጣት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርበታል፤

   ሀ.መድኃኒቱወይም የሕክምና መሣሪያው በብሔራዊ የመድኃኒት ወይም የሕክምና መሣሪያመዘርዝር ዉስጥ የተካተተ ከሆነ፤

   ለ.መድኃኒቱ ወይም የሕክምናመሣሪያው በባለሥልጣኑተገምግሞ የተመዘገበ ከሆነ፤

   ሐ.መድኃኒቱ ወይም የሕክምናመሣሪያዉ ወደ አገር ዉስጥ ሲገባ በምዝገባ ወቅት ከቀረበው መረጃ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ካለው፣

   መ.መድኃኒቱን ወይም የሕክምናመሣሪያዉን ከማስመጣቱ በፊት አስፈላጊ መረጃና ሰነዶችን የያዘ የግዢ መጠይቅ ለባለሥልጣኑ አቅርቦ ሲፈቀድለት፣

   ሠ.የናርኮቲክወይም ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ለማስመጣት ከባለሥልጣኑ የተሰጠ ልዩ ፈቃድ ካለው፣

   ረ.የመድኃኒቱ ወይም የህክምናመሣሪያዉ የመለያ ቁጥር፣ የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ፣እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸዉን መረጃዎች የያዘ ደረሰኝ ሲያቀርብ፤

   ሰ.የሚያስመጣቸዉ መድኃኒቶች ወይም የሕክምናመሣሪያዎች በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ ወይም በሁለቱም ቋንቋዎችየተፃፈ አባሪ ገላጭ ፅሑፍ በማሸጊያዉ ዉስጥ ካለው፤

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር (1) ድንጋጌዎች ቢኖሩም አስገዳጅና አሳማኝ ሁኔታዎችሲያጋጥሙመድኃኒቱ ወይም የሕክምና መሣሪያው ተገምግሞወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባባለስልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## 17. የእንስሳትመድኃኒትወይምየእንስሳትሕክምናመገልገያመሣሪያስለመላክ

1. ማንኛዉምድርጅትየእንስሳትመድኃኒትወይምየእንስሳትህክምናመሣሪያወደዉጪአገርመላክየሚችለው፤

ሀ. መድኃኒቱወይምየህክምናመሣሪያውበባለሥልጣኑየተመዘገበሲሆን፣

ለ. ድርጅቱበባለሥልጣኑየተመዘገበአምራችወይምሕጋዊተወካይሲሆን፣

ሐ.የናርኮቲክ ወይም ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ለመላክ ከባለሥልጣኑ ልዩ ፈቃድ ሲኖረው ብቻ ነው፡፡

2. ማንኛዉምድርጅትየእንስሳትመድኃኒትወይምየእንስሳትህክምናመሣሪያወደዉጪአገርከመላኩ በፊት ከሚላክበት አገር አስፈላጊውን መረጃና ሰነዶች የያዘ የግዢ መጠይቅአቅርቦ በባለሥልጣኑ ማጸደቅና ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 18. የእንስሳትመድኃኒትወይምየእንስሳት ሕክምናመሣሪያግዢናሽያጭ

1. ማንኛዉምድርጅትየእንስሳትመድኃኒትወይምየእንስሳትህክምናመሣሪያመግዛት የሚችለው የታደሰ ፈቃድ ካለው አስመጪ ብቻ ነው፡፡

2. ማንኛዉም ድርጅት የእንስሳት መድኃኒት ወይምየእንስሳት ሕክምናመሣሪያ መሸጥ የሚችለው ከገዢው በፅሁፍ የግዢ መጠይቅ ሲቀርብለት ብቻ ነው፡፡

3. ማንኛዉምአስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅትከሌላበተመሳሳይ ደረጃ ላይ ካለ የእንስሳት መድኃኒትናየእንስሳት ሕክምናመሣሪያ አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅትየእንስሳት መድኃኒትናየእንስሳት ሕክምናመሣሪያዎችን መሸጥም ሆነ መግዛት አይችልም፡፡

4. ማንኛዉምሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትለሌለው ድርጅት የእንስሳት መድኃኒትን ወይም የእንስሳት ሕክምናመሣሪያንመሸጥ ወይምየብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከሌለውድርጅት የእንስሳት መድኃኒትን ወይም የእንስሳት ሕክምናመሣሪያንመግዛት አይችልም፡፡

5. ማንኛዉምሰውየእንስሳት መድኃኒትን ለመሸጥ ወይምለመግዛት የሚችለው መድኃኒቱ በባለስልጣኑ የተመዘገበና በብሔራዊ የመድኃኒት መዘርዝር ውስጥ ያለ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

6. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ወይምየእንስሳት ሕክምና መሣሪያ አስመጪና አከፋፋይ ለሸጣቸው ምርቶች የሽያጭ ደረሰኝ (ኢንቮይስ) የመስጠት ግዴታ ሲኖርበትገዥውም ደረሰኙን ይዞ መገኘት አለበት፡፡

7. የአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 6ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖማንኛውም፡-

ሀ. የእንስሳት መድኃኒት ወይምየእንስሳትሕክምና መሣሪያ በሕገወጥነት ተጠርጥሮ በተያዘበትቅጽበትደረሰኝ (Invoice) ካልቀረበ የእንስሳት መድኃኒቱ ወይም የእንስሳትሕክምና መሣሪያውእንደሕገወጥ ምርት ይቆጠራል፡፡

ለ.የእንስሳት መድኃኒት ወይምየእንስሳትሕክምና መሣሪያበሕገወጥነት ተጠርጥሮ ከተያዘ በኋላ የሚቀርብ ደረሰኝ (Invoice) ተቀባይነት የለውም፡፡

8. ማንኛውም የእንስሳት ጤና ተቋም የእንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ መግዛት የሚችለው ሻጩ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዳለው ሲያረጋግጥ ብቻ ነው፡፡

## ክፍልስድስት

## ስለእንስሳትመድኃኒትናየእንስሳትሕክምናመሣሪያዎችአከመቻቸትናአያያዝስርዓት

### 19. ስለአከመቻቸትናየአያያዝስርዓት

ማንኛዉም የእንስሳት መድኃኒትናየእንስሳትሕክምና መሣሪያ ንግድድርጅትየሚከተሉትን የክምችትና የአያያዝስርዓቶች መከተል አለበት፡፡

1. የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው የእንስሳት መድኃኒቶችናየእንስሳት ህክምናመሣሪያዎችንለባለስልጣኑ በማሳወቅ እስኪወገዱ ድረስ በአግባቡ ቆጥሮና መዝግቦ ማስቀመጥ፣
2. የተበላሹና የመጠቀሚያ ጊዜያለፈባቸው የእንስሳት መድኃኒቶችና የእንስሳት ሕክምና መሣሪያዎች፣ ተቀጣጣይና ብናኝ ነገሮችን እና

ሌሎች በካይ ነገሮችንከመድኃኒትናከሕክምናመሣሪያዉበተለየ ክፍል እንዲከማቹ ማድረግ፣

3. የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ሊያበቃ አጭር ጊዜየቀራቸው የእንስሳት መድኃኒቶችን ቀድሞ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣
4. የፍጆታ መጠንን ከግምት ውስጥ በማስገባት አስፈላጊውን ክምችት መያዝ፣
5. የቅዝቃዜ ሰንሰለት ሊጠበቅላቸው የሚገቡ መድኃኒቶችን በተገቢው የመያዝናየሙቀት ሁኔታንም ቴርሞ ሜትር በመጠቀም መቆጣጠር፣

## 20. ነፃናሙና

1. ነፃናሙናግልጋሎት ላይ መዋል የሚችለዉ ናሙናዉ በባለሥልጣኑ የተመዘገበ የእንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት ህክምናመሣሪያ ከሆነ ወይምልዩ ሁኔታ ሲያጋጥም ለባለሥልጣኑ ቀርቦ ሲገመገምና ሲፈቀድ ነው፣
2. በነፃ ናሙናው ማሸጊያ ላይ የማይሸጥ ወይም በነፃ የሚል ፅሁፍ በእንግሊዝኛ ወይምበአማርኛ ወይም በሁለቱም ቋንቋዎች በግልፅ የተፃፈበት ሊሆን ይገባል፣
3. የናርኮቲክና የሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን በተመለከተ ነፃ ናሙና ሊኖር አይችልም፣
4. ነፃ ናሙናው የእንስሳት መድኃኒቱን ወይም የእንስሳት ሕክምናመሣሪያውን ደህንነት፣ፈዋሽነትና ጥራት ሊቀይር በሚችል ማሸጊያ መታሸግ የለበትም፣
5. ነፃ ናሙና መያዝ ያለበት በተገቢው ባለሙያ ብቻ ነው፣
6. ማንኛዉም በነፃ ናሙና ላይ የሚለጠፍገላጭ ፅሑፍ ግልፅ፣በቀላሉ የሚነበብናየማይበላሽ ሆኖ ስለ መድኃኒቱ ሳይንሳዊና የንግድ ስም፣ ይዘትና መጠን፣ መለያ ቁጥር፣ የአምራች ስምና አገር፣ የአገልግሎት

ማብቂያ ጊዜ፣ የአያያዝ ሁኔታን የሚገልፅ በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ ወይም በሁለቱምቋንቋዎችመረጃ መያዝ አለበት፡፡

## 21. ስለመዝገብአያያዝናሪፖርትአደራረግ

ማንኛዉምየእንስሳትመድኃኒትናየእንስሳትየህክምናመሣሪያንግድድርጅትየሚከተሉት ንሰነዶችየመያዝናእንደአግባቡለባለስልጣኑሪፖርትየማድረግግዴታአለበት፤

1. ዝርዝር ኢንቮይሶችን፣ደረሰኞችን፣የክምችት መቆጣጠሪያ ስቶክና ቢን ካርዶችንናየመሳሰሉትንዝርዝርመረጃዎችን ማዘጋጀትና በአግባቡ የመያዝ፣
2. የቀን ሽያጭ መዝገብ በአግባቡ የመያዝ፣
3. የሸጠለትን ወይም የገዛበትን ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ፣ደረሰኞችንና ሌሎች መረጃዎችንየመያዝ፣
4. ለገዥው ደረሰኝ የመስጠትና ቀሪውን የመያዝ፣
5. በግዥው መጠይቅ ላይ የገዥውን ድርጅት ማህተም ያለበትን ደረሰኝ የመያዝ፣
6. ናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክመድኃኒቶች የግዥና የሽያጭ ሰነዶች ቁልፍ ባለዉ ሳጥን ቆልፎ የመያዝ፣
7. ከባለሥልጣኑየሚደርሱትንመመሪያዎችና ደረጃዎች በአግባቡ የመያዝና የመተግበር፣
8. ለሽያጭ በቀረቡ የእንስሳት መድኃኒቶችናየእንስሳትህክምናመሣሪያዎች መያዣ ላይ የአምራች ድርጅቱን ስምና አድራሻ የመፃፍ፣
9. ወደ አገር ውስጥ ስለገቡ፣ስለተከፋፈሉናስለተከማቹእንዲሁም ስለተላኩ የናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክመድኃኒቶች መረጃን በመያዝ በየስድስትወሩለባለሥልጣኑ ሪፖርትየማድረግ፣
10. በተለያየ ምክንያት የተወገዱ ወይም ጥቅም ላይ የማይውሉ የእንስሳት መድኃኒቶች ወይምየእንስሳትህክምና መሳሪያዎች የተወገዱበትን የምስክር ወረቀት በአግባቡ የመያዝ፣

11.የተሸጡ የእንስሳት መድኃኒቶችናየእንስሳትህክምናመሣሪያዎችን መረጃ የያዙ ሰነዶችማስዉ፹□ አስ□ላፂ ሆኖ ሲቶኝባለስልጣኑንበማሳወቅከአንድ ዓመትባላነሰ ቿ□ በማስቀመዓ እንዲወገዱ□ማትረፅ፣

12.አስመጪ ድርጅት ወደ አገር ዉስጥ አስገብቶ ያከፋፈለዉ የእንስሳት መድኃኒት ወይምየእንስሳትሕክምና መሳሪያ የተበላሸ መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም ጥርጣሬ ሲኖረው በአስቸኳይ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ እና በራሱ ወጪ ከገበያ የመሰብሰብ፣

13.በእንስሳት መድኃኒትና በእንስሳትሕክምና መሳሪያ ላይ የታዩ ጎጂ ባሕርያትና የጥራት ለዉጥ ችግር መከሰቱን ሲያዉቅ ወይም ሲጠራጠር ወይም ሲሰማ ስለጉዳዩ በአስቸኳይ ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ፡፡

## ክፍልሰባት
## አስተዳደራዊእርምጃዎች

### 22. በጠቅላላው

1. ባለስልጣኑ ይህንን መመሪያ በመተላለፍ ሲሠራ የተገኘ ድርጅትን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል።
2. ማንኛውምድርጅትየፈፀመውጥፋትየብቃትማረጋገጫምስክርወረቀቱንየማያሳግድ ወይም የማያሰርዝእንዲሁምበወንጀልየማያስጠይቅከሆነባለስልጣኑበመጀመሪያየቃልቀጥሎምየፅሁፍማስጠንቀቂያሊሰጠውይችላል::
3. ድርጅቱበተሰጠውማስጠንቀቂያመሰረትአስፈላጊውንየእርምትእርምጃካልወሰደባለስልጣኑበቅደምተከተልየሚከተሉትንአስተዳደራዊእርምጃይወስዳል::

ሀ. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ማገድ

ለ. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን መሠረዝ

### 23. የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀትስለማገድ

1) በዚህ ክፍል በአንቀጽ 22 □ተደነገገውእንደተጠበቀ ሆኖማንኛዉም ድርጅትከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ማስጠንቀቂያ

መስጠት ሳያስፈልግ ከሶስት ወር እስከ አንድ ዓመት በሚ□ርስ ቲ□የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱንባለስልጣኑሊጸግትበት ይችላል፡፡

ሀ. □ባለሥልጣኑን ተቆ□□ሪ □ቱዓዓር ተፅባሩን እንዳያከናዉን እንቅፋት □□□ረእንደሆነ፣

ለ. የብቃት ማረ□ቱ□ ምስ□ር ወረቀት ለማ□ስ □ሚጸስ□ልቶመሰረታዊመስፈርቶችሲጓደሉ፤

ሐ. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጣቸዉ ተቋማት ዉጪ የንግድ ግንኙነት ካደረገ፣

መ. ሕጋዊየብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከሌለዉ ድርጅትየእንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት ሕክምናመሳሪያ ካስመጣ፣ ከገዛ ወይም በማንኛዉም መንገድ ተቀብሎ ካከፋፈለ ወይም ከሸጠ፣

ሠ.ፈቃድ ከተሰጠዉ ወይም በአግባቡ ከተወከለ ባለሙያ ዉጪ የእንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ ማስመጣት፣መላክ ፣ ማከፋፈል ወይም መሸጥ፣

ረ.ተንቀሳቃሽ ሽያጭ ማከናወን፣

ሰ. በአዕምሮ ሕመም ወይም ሊያሰራ በማይችል ዓይነት የአካል ጉድለት ወይም ከመጠን በላይ የአልኮል መጠጥ፣ የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሐኒቶችንወይም ሌላ ምጥን በመዉሰድ በሚመጣ የአዕምሮ ህመም ምክንያት ወይም በእድሜ መግፋትምክንያት ተግባሩን በአግባቡ ማከናወን የማይችል ባለሙያን ማሰራት፣

ሸ.ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ላልተሰ□ዉተጠቃሚ ግለሰብ መሸጥ፣

ቀ.ነፃ ናሙና ከሸጠ፣

በ. ከባለስልጣኑፈቃድሳያገኝየአገልግሎት ወይም የስምወይምየአድራሻለዉዓ ያደረገ ከሆነ፣

ተ. የሙያስራፈቃድየሌለውንና አግባብ ባለው አካልፈቃዱ □ታገደበትን ወይም የተሰረዘበትን ባለሙጸ ካሰራ፡፡

2) ድርጅቱ አግባብ ባለው አካል የታገደ እንደሆነ ባለስልጣኑ ድርጅቱ አግባብ ካለው አካል በንግድ ስራእንዲሰማራ እስኪፈቀድለት ድረስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ያግዳል፡፡

3) ባለሥልጣኑ ድርጅቱሊታገድ የቻለበትን ምክንያትና የተወሰደውን እርምጃ ለድርጅቱ በፅሁፍየማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 24. የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀትስለመሰረዝ

1. ማንኛዉምድርጅትከሚከተሉትምክንያቶችበአንዱጥፋተኛሆኖከተገኘባለስልጣኑ የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀቱንሊሰረዝይችላል፡፡

   ሀ.ያልተመዘገበ ወይም የተከለሰ ወይምየተጭበረበረ ወይም ተመሳስሎ የቀረበ ወይምበሕገወጥ መንገድ ወደ ሀገር ዉስጥ የገባ ወይምምንጩ ያልታወቀ ወይምህጋዊ የግዥ ሰነድ የሌለው ወይምገላጭ ጽሁፍ የሌለዉ ወይምአሳሳች ገላጭ ጽሁፍ የያዘ የእንስሳት መድኃኒት ወይም የሕክምና መገልገያ መሣሪያ ከሸጠ ወይም ካከፋፈለ ወይም

   ለ.በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23 የተጠቀሱትንእገዳየሚያስከትሉ ተመሳሳይ ተግባራትንከሁለትጊዜበላይፈጽሞ ከተገኘ ወይም

   ሐ.□ብቃትማረ□□ ምስ□ር ወረቀቱን ያገኘዉ በማታለል □□ም □ሀሰት መረ□በማቅረብ መሆኑከተረጋገጠ ወይም

መ.የተሰጠውንየብቃት ማረጋገጫ ምስ□ር ወረቀት ለሌላ ሰ□መጠቀሚያነት አሳልፎ ከሠጠ ወይም

ሠ.የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23 መሠረትታ□□ □እጸለትር□ቱ አገል□ሎትመስ□ቱንከቀ□ለ ወይም

ረ.የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከሚፈቅድለት ውጪ ማናቸውንም አይነት ተጨማሪ አገልግሎት ከሰጠወይም

   ሰ.ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ በአምራቹ ታሽገዉ የመጡ የእንስሳት መድኃኒቶችና የእንስሳት ሕክምና መሣሪያዎችን እንደገና እያሸገ ሲሸጥ ከተገኘ ወይም

   ሸ.የተበላሸ ወይም የአገልግሎት ዘመኑ ያለፈበት ወይም ገበያ ላይ እንዳይዉል የታገደ የእንስሳትመድኃኒት ወይም የእንስሳት የሕክምና መሣሪያ ከሸጠ ወይም ካከፋፈለ፡፡

2. ድርጅቱ ስራውን በራሱ ፈቃድካቋረጠባለስልጣኑየብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ይሰርዛል፡፡

3. ድርጅቱ አግባብ ካለው ሌላ አካል በንግድ ስራ ላይ እንዳይሰማራ የንግድ ፈቃዱመሰረዙከተረጋገጠ ስረዛው ተነስቶለት በንግድ ስራ ዳግመኛ እንዲሰማራ እስኪፈቀድለት ድረስ ባለስልጣኑ የሠጠውየብቃት ማረጋገጫ ምስ□ር ወረቀት ይሰረዛል፡፡ ነገር ግንባለስልጣኑ ይህንን እርምጃ ሲወስድ ለድርጅቱበንሁአ □ማሣወቅ ግዴታ አለበት::

## 25. የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀትእገዳናስረዛንስለማንሳት

የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ማንኛውምድርጅት የተጣለበት እገዳ ወይም ስረዛ ሊነሳለት የሚችለው በዚህ መመሪያ አንቀፅ (28) መሰረት ቅሬታ ካቀረበ እና ቅሬታው ተቀባይነት አግኝቶ እገዳዉ ወይም ስረዛዉ እንዲነሳለት ሲወሰን ብቻ ነው፡፡

## 26. የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀትስለመመለስ

ማንኛዉም ድርጅት፤

1. ቀትሞ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠበት የአገልፅሎት □ይነት ወይም ቦታ ው□ም የአገልግሎት □ረጽ □ለወ□ እንደሆነ እና□አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማፅኘት ያለበት ሲሆንወይም
2. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ከታገደ ፣ ከተሰረዘ ወይም ሳይታደስ ከቀረ፤ወይም
3. የሚሰጠዉ አገልግሎት ለእንስሳትና ሕብረተሰብ ጤና አደገኛ ነዉ ብሎ በባለሥልጣኑ ከታመነ ወይም ድንገተኛየጤና ችግር ሊፈጥር ይችላል ተብሎ ከታመነ፤የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀቱን በሁለት ቀናት ዉስጥ ለባለስልጣኑ መመለስ አለበት፡፡

## 27. የእንስሳትመድኃኒትናየእንስሳትሕክምናመሣሪያንስለማስተላለፍ

1. እገዳወይምስረዛየተጣለበት ወይም ስራውን በራሱ ፈቃድ ያቋረጠ ማንኛውምድርጅትበእጁያሉአገልግሎትላይመዋልየሚችሉየእንስሳትመድኃኒቶችናየ እንስሳትሕክምናመሣሪያዎችን፣□ፅ□ ኢንቮይሶችን፣መዝገቦችንና ማዘዣ

ወረቀቶችንባለስልጣኑንበማስፈቀድየብቃትማረጋገጫምስክርወረቀትላላቸው ሌሎች ድርጅቶችመሸጥ ወይምማከፋፈልወይምማስተላለፍአለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሠው እንደተጠበቀ ሆኖ ስራውን ያቋረጠ ድርጅት የእንስሳት መድኃኒቶቹንና የእንስሳት ህክምና መሳሪያዎቹን ከባለስልጣኑ ፈቃድ ውጪ ለሌሎች ድርጅቶች ማስተላለፍ አይችልም፡፡

## 28. ስለቅሬታአቀራረብ

1. ማንኛዉምሰዉ ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ፣ እድሳት፣እገዳና ስረዛ ወይም ሌሎች ባለሥልጣኑ የሚወስዳቸዉ እርምጃዎችን በተመለከተቅሬታ ካለው በየደረጃው ላሉ የበላይ ኃላፊዎች ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በየደረጃው ላሉ የበላይ ኃላፊዎች ቅሬታውን አቅርቦ በውሳኔው ያልረካ ማንኛውም ሠው የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት በሚያዘው መሠረት ቅሬታውን ባለስልጣኑ ላቋቋመው ቅሬታ ሰሚ አካል ማቅረብ ይችላል፡፡
3. ከአንድ ወር በኃላ የሚቀርቡ ማንኛውም ዓይነት ቅሬታዎች ተቀባይነት የላቸውም፡፡

# ክፍልስምንት

## ልዩልዩድንጋጌዎች

## 29. መረጃንይፋስለማድረግ

1. በተረጋገጡ ተጨባጭ ጥቆማዎች በማንኛውም ድርጅትውስጥ የአሰራር ግድፈቶችን ወይም ሌሎች የህብረተሰቡንና የእንስሳት ጤናን አደጋ ውስጥ የሚጥሉ ጥፋቶችን ካገኘ ባለሥልጣኑለሕብረተሰቡ አመቺ በሆኑ የመገናኛ ዘዴዎች መረጃዎቹንይፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑአስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የታገደበት፤ የተሰረዘበትን ወይም ሳያሳድስ የቀረ ድርጅትን በተመለከተ መረጃዎች ለህብረተሰቡ እንዲደርሱ ሊያደርግ ይችላል፡፡

3. በባለሥልጣኑምስጢርተብለው ከተያዙትበስተቀርማንኛውም ሰው ስለ ማንኛውም ድርጅት የሚፈልገውን መረጃ የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

## 30. የአግልግሎትክፍያ

ማንኛዉምድርጅት አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትለማዉጣት ወይምለማሳደስ ወይም ምትክ ለማግኘት እንዲሁም ባለስልጣኑ ለሚያካሂደው የቅድመ ፈቃድ ምርመራ (Inspection) ስራ የሚከተሉትን የአገልግሎት ክፍያዎች ለባለስልጣኑ መክፈል ይኖርበታል፤

| የድርጅቱ ዓይነት | አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማውጣት | ለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እድሳት | ምትክ ለማግኘት | ለ2ተኛ ዙር ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን | ለ3ተኛ ዙር ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን | የባለሙያ ለዉጥ | የቦታ ለዉጥ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የእንስሳት መድኃኒትና የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ አስመጪ | 720 | 360 | 120 | 720 | 1440 | 360 | 360 |
| የእንስሳት መድኃኒትና የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ ሳኪ | 720 | 360 | 120 | 720 | 1440 | 360 | 360 |
| የእንስሳት መድኃኒትና የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ ጅምላ አከፋፋይ | 600 | 300 | 120 | 720 | 1440 | 360 | 360 |
| የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ አስመጪ | 600 | 300 | 120 | 720 | 1440 | 360 | 360 |
| የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ ጅምላ አከፋፋይ | 600 | 300 | 120 | 720 | 1440 | 360 | 360 |

## 31. ተፈፃሚስለማይሆኑሕጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማናቸዉም መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡

## 32. መመሪያውየሚጸናበትጊዜ

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ፣ ታህሳስ2006 ዓ.ም**

**□ርማ፡-------------**

**ጠርዙ ዳያደጋ (ዶ/ር)**

**የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን**
**ዋና ዳይሬክተር**

## ዕዝል1

**የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መሣሪያ ንግድ ድርጅት ለማቋቋም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መጠየቂያ ማመልከቻ ቅጽ**

1. የአመልካች ስም ከነአያት_______________________________

2. የአመልካች መኖሪያ አድራሻ

ክልል __________ዞን _____________ወረዳ

_____________ከተማ_________________ክፍለ ከተማ

__________________ቀበሌ ______________የቤት ቁጥር ______________

3. ሊቋቋም የታሰበዉ የእንስሳትመድኃኒትና የሕክምና መሣሪያ ንግድ ድርጅት ዓይነት

ሀ. የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መሣሪያ አስመጪ፣

ለ. የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መሣሪያ ጅምላ አከፋፋይ፣

ሐ. የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ አስመጪ

መ. የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መሣሪያ ላኪ፣

4. ድርጅቱ የሚያስመጣቸዉ ወይም ጅምላ የሚያከፋፈላቸዉ ወይም የሚልካቸዉ'

ሀ. የእንስሳት መደኃኒትና የሕክምና መሣርያ ☐

ለ. የእንስሳት ሕክምና መሣርያ ☐

ሐ. ለሎች ካሉ ይጠቀስ .------------------------------------------

5. የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መሣሪያ ንግድ ድርጅቱባለቤትነት

ሀ. የግል

ለ. ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት

ሐ. የአክሲዮን (አስረጂ መረጃዎች ይያያዝ)

6. የእንስሳት መድኃኒትናየሕክምና መሣሪያንግድ ድርጅቱ ሊቋቋም የታሰበበት አድራሻ፣

ክልል __________ዞን___________ከተማ_____________

ክፍለ ከተማ___________ ወረዳ___________ ቀበሌ________የቤ/ቁ_________

7.አመልካቹ/ቿ በድርጅቱ የሚኖረዉ/ራት ኃላፊነት፣

ሀ. ባለንብረት

ለ. ባለንብረትና ባለሙያ

8. ድርጅቱንየሚመራዉ ባለሙያ

ሀ. ስም ከነአያት ________________________________

ለ. የሙያ ደረጃ ________________________________

ሐ. የሙያ ምዝገባ ፈቃድ ቁጥር ________________________________

መ. በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለዉ አካል

የተመዘገበ____________________________________________________

(ባለሙያዉ ተቀጣሪ ከሆነ የዉል ስምምነት ይያያዝ)

ሠ. ባለሙያዉ በሙያዉ (በዘርፉ) ያለዉ የሥራ ልምድ (መረጃ ይያያዝ)

9. የቴክኒክ ረዳት/መጋዘን ኃላፊ ባለሙያ

ሀ. ስም ከነአያት ________________________________

ለ. የሙያ ደረጃ ________________________________

ሐ. የሙያ ምዝገባ ፈቃድ ቁጥር ________________________

መ. በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተመዘገበ

________________________________

(ባለሙያዉ ተቀጣሪ ከሆነ የዉል ስምምነት ያያይዝ)

ሠ.ባለሙያዉ በሙያዉ (በዘርፉ) ያለዉ የሥራ ልምድ (መረጃ ይያያዝ)

10. የሚቋቋመዉ ድርጅት

ሀ. የዉሃ አገልግሎት

አለዉ ☐ የለዉም ☐

ለ. የኤሌክትሪክ መብራት አገልግሎት

አለዉ ☐ የለዉም ☐

ሐ. ለትራንስፖርት አገልግሎት ምቹ

ነዉ ☐ ደለም ☐

መ. የስልክአገልግሎት

አለዉ ☐ የለዉም ☐

ሠ. የፖስታአገልግሎት

☐ ☐

አለዉ የለዉም

ረ. አረካካቢዉ ለእንስሳት መድኃኒት ወይም የሕክምና መሣሪያ ንግድ ተግባርተስማሚ

ነዉ አይደለ

ሰ. ኢሜል አድራሻ አለዉ

አለዉ ለዉም

11. ድርጅቱ፣

ሀ. የማረካከቢያክፍል ስፋት

ለ. የማከማቻ ክፍል ስፋት

ሐ. የማከማቻ ክፍሎች በቂ መደርደሪያ፡ አለዉ የ ዉም

መ. የማረካከቢያ ክፍል ማረካከቢያ ጠረጴዛ፡ አለው የለዉም

ሠ. ማቀዝቀዣ ከነሙቀት መቆጣጠሪያዉ ቴርሞሜትር፡

አለዉየለዉም

ረ. የእሳት አደጋ መከላከያ (ማጥፊያ)

አለዉየለዉም

ሰ. ለጽህፈት ሥራ የሚጠቀምበት ጠረጴዛና ወንበሮች

አለዉየለዉም

ሸ. የልብስ መስቀያ

አለዉየለዉም

ቀ. የማይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ማስቀመጫ ቁልፍ ያለዉ ካቢኔት

አለዉየለዉ

በ. መፀዳጃ ክፍል ከነዉሃ አገልግሎቱና የእጅ መታጠቢያ ሲንክ

አለዉየለዉም

ተ. ድርጅቱ ጎርፍ የማያስገባ

ነዉ ☐ አይደለም ☐

ቸ. ድርጅቱየሚቋቋምበት ቤት ቆሻሻ የሌለበት አካባቢ

ነዉ ☐ አይደለም ☐

ነ. ደረቅቆሻሻማስወገጃ

አለዉ ☐ የለዉም ☐

11. እኔ ከዚህ በላይ የዘረዘርኳቸዉ መረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸዉን አረጋግጣለሁ

ስም________________________________________

ፊርማ____________ቀን____________________

## ዕዝል 2

<u>የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መሣሪያ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማዉጣት የሚጠይቁ ግለሰቦች አስፈላጊዉን ደረጃና መመዘኛ ማሟላታቸዉን ለማረጋገጥ በባለሙያዎች የሚሞላ የመገምገሚያ ቅፅ</u>

1. የድርጅቱ ስምና ዓይነት____________________________________

2. አድራሻ

ክልል__________ ዞን__________ ክ/ከተማ__________ ወረዳ_________

የቤ.ቁ__________ ስ.ቁ_______________ ፖስታ___________________

ሞባይል.ቁ_____________ ፋክስ.ቁ.____________ ኢ.ሜል______________

3. የባለንብረቱ ሙሉስም _____________________________________

4. በስሙ ፈቃድ የተሰጠዉ ባለሙያ

ሀ. ስም ከነአያት_______________________________________

ለ. የሙያ ደረጃ ____________ የአገልግሎት ዘመንና ስራ ልምድ________

ሐ. የሙያና ምዝገባ ፈቃድ ቁጥር__________________

5. ረዳት ባለሙያ

ሀ. ስም ከነአያት___________________________

ለ. የሙያ ደረጃ ____________ የአገልግሎት ዘመንና ስራ ልምድ________

ሐ. የሙያና ምዝገባ ፈቃድ ቁጥር _______________________________

6. ድርጅቱ የሚያስመጣቸዉ ወይም በጅምላ የሚያከፋፍላቸዉ

ሀ. የእንስሳት መድኃኒቶች፣ሕክምና መሣሪያዎች ☐

ለ. የእንስሳት ሕክምና መሣሪያዎች ☐

ሐ. ለሎች ካሉ ይጠቀስ ______________________________

7. የሚቋቋመዉ ድርጅት

ሀ. የዉሃ አገልግሎት

አለዉ☐ የለዉ☐

ለ. የኤሌክትሪክ መብራት አገልግሎት

አለዉ☐ የለዉ☐

ሐ. ለትራንስፖርትአገልግሎትምቹ

ነዉ ☐ አይደለም ☐

መ. የስልክ አገልግሎት

አለዉ☐ የለዉ☐

ሠ. የፖስታ አገልግሎት

አለዉ☐ የለዉ☐

ረ. አካባቢዉለእንስሳት መድኃኒትወይምየሕክ/መገ/መሳሪያንግድተግባር ተስማሚ

ነዉ      አይደለም ☐ ☐

ሰ. ኢ.ሜልአድራሻአለዉ

አለዉየለዉም ☐ ☐

ሸ. የመፀዳጃ ክፍል ከዉሃ አገልግሎትና የእጅ መታጠቢያ ሲንክ

አለዉየለዉም ☐ ☐

8. ድርጅቱ የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መሣሪያዎች

1. ማከማቻ ክፍል

ሀ. የማከማቻ ክፍሉ የተለያዩ ክፍሎች ካሉት ስፋታቸዉና ብዛታቸዉ ይገለጽ

ለ. በቂ መደርደሪያ

አለዉ ☐ የለዉም ☐

ሐ. ማቀዝቀዣ ከነቴርሞ ሜትር

አለዉ ☐ የለዉም ☐

መ. የግድግዳ ቴርሞሜትር

አለዉ ☐ የለዉም ☐

ሠ. የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች መያዣ ባለቁልፍ ቁምሳጥን

አለዉ ☐ የለዉም ☐

ረ. ሌሎች ካሉ ይገለጽ_______________________________

2. ማረካከቢያ ክፍል

ሀ. የማረካከቢያ ጠረጴዛ

አለዉ ☐ የለዉም ☐

ለ. ማሸጊያ ቁሳቁስ ካለዉ ይገለጽ______________________

3. የቴክኒክ ክፍል ኃላፊዉ ቢሮ

ሀ. ጠረጴዛ፣ ወንበርና ከምፒዉተር

አለዉ ☐ የለዉም ☐

ለ. የተለያዩ መረጃዎች ማስቀመጫ ባለቁልፍ ቁምሳጥን /ካቢኔት

አለዉ ☐ የለዉም ☐

4. የተለያየ የአስተዳደር ቢሮ

አለዉ ☐ የለዉም ☐

ሀ. የመጸዳጃ ክፍል ከነዉሃ አገልግሎትና የእጅ መታጠቢያ ሲንክ

አለዉ ☐ የለዉም ☐

ለ. ሁሉም ክፍሎች በአንድ ህንፃ

ናቸዉ ☐ አይደሉም ☐

9. የድርጅቱ ዲዛይንና አሰራር

ሀ. የተለያዩ ክፍሎች ወለል ሁኔታ ይገለጽ------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------

ለ. የክፍሎች ግድግዳ የተሰራበትና ሌላ ሁኔታ ይገለጽ----------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------

ሐ. የክፍሎች ጣሪያ ኮርኒስ

አለዉ ☐ የለዉም ☐

መ. ክፍሎች በቂ ብርሃንና የአየር ዝዉዉር

አላቸዉ ☐ የላቸዉም ☐

ሠ. የድርጅቱ አሰራር ከመሬት ከፍታ ኖሮት ጎርፍ የሚያስገባ

ነዉ ☐ አይደለም ☐

ረ. መዝጊያዎች በሙሉ ይሰራሉን

አዎ ☐ የለም ☐

ሰ. የፍሳሽ ማስወገጃ

አለዉ ☐ የለዉም ☐

10. የክፍሎች አሰራር ከአቧራና ከልዩ ልዩ ነፍሳት የተጠበቀ፣ ለመጽዳትና ንጽህናዉን ለመጠበቅ አመቺ

ነዉአይደለም ☐ ☐

11. ስለድርጅቱ ሌሎች ያልተገለፁ ሁኔታዎች ካሉ ዝርዝር ሁኔታዉ ይገለጽ________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

12. ስሙ ከላይ የተጠቀሰዉ ድርጅት በ________ቀን_________ ዓ.ምበ______ሰዓት ተገኝተን አስፈላጊዉን ቁጥጥር በማድረግ ድርጅቱን በሁሉም ሁኔታ የተሟላ/ያልተሟላ መሆኑን አረጋግጠናል፣ ስለሆነም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጥ እንደግፋለን/እንደግፍም፡፡

ባለሙያዎች ስምሙያ ፊርማ ቀን

1. ______________________________ __________
2. ______________________________ __________
3. ______________________________ __________

13. የቡድን መሪ አስተያየት

______________________________________________

______________________________________________

ሙሉ ስም______________________________

ፊርማ ____________________

ቀን______________________

14. የኃላፊዉ ዉሳኔ

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

ሙሉ ስም______________________


ፊርማ ____________________

ቀን__________________


## ዕዝል 3

1. የእንስሳት መድሐኒትና የሕክምና መሳሪያ ማካማቻ ክፍል የዲዛይንና ሌይ አውት ሞዴል

5 m



10m




- የማካማቻ ክፍሉ ስፋት ቢጸንስ 50 ካሬ ሜትር  መሆን አለበት
- የማካማቻ ክፍሉ ቁመት ቢያንስ 2.7 ሜ መሆን አለበት
- ማንኛውም ዓይነት የእንስሳት መድሐኒትና የሕክምና መሳሪያበመደርደሪያ ወይም ፓሌት ብቻ መቀመጥ አለበት
- በዚህም ማንኛውም የእንስሳት መድሐኒትና የሕክምና መሳሪያንግድ ድርጅት ማከማቻ የሚያዘጋጀው ማከማቻ ክፍል በመመሪያው ላይ የተቀመጡት የመደርደሪያ ወይም ፓሌት አቀማመጥ መስፈርት ማሟላት አለበት

- በዚህ መሰረት በአንድ የእንስሳት መድሐኒትና የሕክምና መሳሪያማከማቻ ክፍል በመስፈርቱ መሰረት ሊኖሩ የሚችሉ  መደርደሪያ ወይም ፓሌት ብዛት ከዚህ በታች በተቀመጠው ስሌት መሰረት ማወቅ ይቻላል፡፡

ለምሳሌ በስእሉ ላይ እንደተቀመጠው የመጋዘኑ ስፋት 10ሜትር በ 5 ሜትር የሆነ ማከማቻ ክፍል ሊኖሩ የሚችሉ መደርደሪያዎች ወይም ፓሌቶች ለማወቅ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

$$\text{Total Area} = \text{width*length}$$

$$(\text{Area}_1) = 10\text{m*5m}$$

$$= \underline{50\text{m}^2}$$

ይሁን እንጂ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት አንድ የእንስሳት መድሐኒትና የሕክምና መሳሪያመደርደሪያ ወይም ፓሌት ሊቀመጥ የሚችለው ከማከማቻ ክፍሉ ግድግዳ ቢያንስ 20 ሴ.ሜ ርቆ መቀመጥ አለበት፡፡

በዚህ መሰረት ከግድግዳው በአራቱ አቅጣጫ ያለው /20cm*4 side/ ስፋት ከጠቅላላ የመጋዘኑ ስፋት መቀነስ አለበት፡፡በዚህ መሰረት

$$\text{Area}_2 = \text{width}_2\text{*length}_2$$

$$= (\text{width}_1\text{-(20cm*2))*(length}_1\text{-(20cm*2))}$$

$$= (10\text{m-0.4m})*(5\text{m-0.4m})$$

$$= 9.6\text{m*4.6m}$$

$$= \underline{44.16\text{m}^2}$$

ስለዚህ የእንስሳት መድሐኒትና የሕክምና መሳሪያመደርደሪያዎቹ በውስጠኛው ስፋት ($\text{Area}_2$) ላይ ብቻ ናቸው ሊቀመጡ የሚችሉ፡፡

በዚህ መሰረት በማከማቻ ክፍሉ በ $\text{Area}_2$ ላይ ሊኖሩ የሚችሉ የመደርደሪያ ብዛት ለማወቅ

$$\textit{No of shelves/ Pallets} = \frac{\textit{Area}_2}{\textit{Area of shelves + Area of free space}}$$

$$\frac{44.16\ m^2}{(1m*4.6m) + (1m*4.6m)} = \underline{4.8\ \text{shelves / pallets}}$$

*በዚህ መሰረት በ 50m² ስፋት ያለው መጋዘን ሊኖሩ የሚችሉ (1m width & 4.6m length ያላቸው ሸልፎች) የሸልፍ ብዛት 5 ሼልፎች ብቻ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡*

2. **የማረካከቢ ክፍል ስፋት**

   የክፍሉ ስፋት 9 ካሬ ሜትር ሲሆን የአነስተኛው ጎን ርዝመት ቢያንስ 2.5ሜ መሆን አለበት